የ1966 አብዮት ሃይማኖትን ከመንግስት በማፋታት ለኢትዮጵያ ህዝብ ትልቅ ውለታ ውሏል። ይህ በጎ ጅምር ቀጥሎ ከግንቦት ወር 1983 ዓ·ም በኋላም የብሔር ብሔረሰቦች መብት በሕገመንግስት ደረጃ የደነገገ የሃይማኖት እኩልነት እና ነፃነት ታወጀ። የአሁኑ ሕገመንግስትም በግልጽ ካስቀመጣቸው አብይ ነጥቦች መካከል አንዱም ይህ ነው። መጪው የጋራ ዕድላችን መመስረት ያለበት ከታሪካችን የወረስነውን የተዛባ ግንኙነት በማረም እና የጋራ ጥቅማችንን በማሳደግ ላይ መሆኑን መቀበል:: (የሕገመንግስቱ መግቢያ) ስለሆነም ከትምህርት ሚኒስትር የሙስሊሙን የትምህርት ሁኔታ ማሻሻል የሚያስችሉ አዎንታዊ እርምጃዎችን ስንጠብቅ እየተሰማ እና በተግባር እየታየ ያለው የነበረውን የሚንድ ከሙስሊምነቱ አልያም ከትምህርቱ አንዱን እንዲመርጥ የሚያስገድድ ደንብ እየተዘጋጀለት እንደ ኻነ ነው። ይህ ደንብ ምክንያታዊ በሚመስል መልኩ ተዘጋጅቶ ወደ ግፍ ዘመን ሊመልሰን መሆኑን ስንረዳ ዝምታውን መስበር እንዳለብን ተሰማን። ደንቡ

ሕገመንግስቱን አስታኮ እና የመንግስትን ሴኩላርነት አመካኝቶ መቅረቡ ደግሞ ይበልጥ ይሠቀጥጣል።

በመሠረቱ የሕገ መንግስቱን አንቀጾች በጥልቀት ለመረዳት ስለ ሴኩላሪዝም ጠቅለል ያለ ግንዛቤ መጨበጥ ይገባል። አለማዊ (Secular) መንግስት እና ዓለማዊ (Secularism) የሚሉት ታላቅ የተለያዩ ትርጉም የሚሰጡ ነገር ግን በአንድነት አብረው የሚጓዙ ጽንሰ ሐሳቦች ናቸው። "ዓለማዊነት" ከሃይማኖታዊ መንገድ የተለየ የሕይወት ንድፈ ሐሳብ ወይም ሃይማኖት ስለ ሕይወት የሚሰጠው ፍልስፍና የተለየ የራሱን የሕይወት ፍልስፍና የሚያስቀምጥ ርዕዮተ አለም ነው። ዓለማዊ መንግስትን እና ሃይማኖትን የሚያገናኙ በርካታ መስኮች አሉ።መንግስት በሕዝብ በተሰጠው ሥልጣን ሕዝብን ወክሎ የሚሰራው ሥራ እና አካሄዱ አንድን ሃይማኖት ከሌላው  አልያም የአንዱንዓይነት ሃይማኖተኝነት ከሌላው ሃይማኖተኝነት የሚያበላልጥ መሆን አይገባውም መኾን አይገባውም። የማንኛውም አገር ሴኩላሪዝም ከገዛ ራሱ ታሪካዊ እና ተጨባጭ እውነታ እና በየአገሩ ካለው ነባራዊ እውነታ አንጻር የሚገመገም

ነው።ዓለም አቀፋዊ ይዞታ ያላቸው ለሴኩላር መንግስት መወለድ መሥፈርት የሚኾኑ ነጥቦችን ማስቀመጥ አዳጋች እንደ ኾነመረዳት ይቻላል።

## ከሃይማኖት እና መንግስት ቀጥሎ

የሴኩላሪዝም ዓይነተኛ መገለጫው የትምህርት ፖሊሲው እና ሥርአቱ ነው። ሴኩላሪዝም የትምህርት አላማዎች እና ይዞታዎች ዓለማዊ መሆን እንደሚኖርባቸው ያስቀምጣል። በስርዐተ ትምህርት ውስጥ አንድን ሃይማኖት ብቻ የሚያንጸባርቅ አንድን ሃይማኖት (ሃይማኖተኝነትን) ለሌላኛው የሚያበላልጥ ነጥብ አለመኖሩን ማረጋገጥ ይገባዋል። ከዚህ በተጨማሪ በመደበኛ የትምህርት ወቅቶች በክፍል ውስጥ እንደ ጸሎት እናየቅዱስ መጽሐፍ ንባቡ ያሉ ሃይማኖታዊ ተግባራትን የመከልከል ሐላፊነት አለበት። በሌላ በኩል ከትምህርት ጋር በተያያዘ የሃይማኖት ተቋማትን ስናይ ዓለማዊ መንግስት ሃይማኖታዊ ተቋማትን የመመሥረት(የመርዳት) ሐላፊነት የለበትም።

የሃይማኖታዊውን ተቋም ዓለማዊ ጎኖች ግን ሊከታተል እና ሊደጉም ይችላል። እንደ አገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ

እና እንደ ተቋሙ ዓይነት እገዛ በማድረጉ አዎንታዊ ጣልቃ ገብነት ሊኖረው ይችላል።

ዓለማዊ መንግስት በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የሚደረጉ ስብስቦችን በሚመለከት ልክ እንደ ማንኛውም የስብስብ ዓይነት አድርጎ በመቁጠር የመገናኛ እና የሃይማኖት ተግባራትን የመፈጸም ቦታዎችን ሊያመቻች ይችላል።አልያም በተመቻቸው ቦታ ላይ እነዚህ ተግባራት እንዲፈጽም ሊፈቅድ ይችላል። ለአብነት ያህል በአሜሪካ ለሚገኙ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች በኮንግረሱ ዘማካይነት ከወጡ ድንጋጌዎች እ·ኤ·አ በ1984 የተላለፈውን "የእኩል ተጠቃሚነት ደንብ"(Equal Access Act) ማየት ይቻላል። በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ደግሞ ሁኔታው ለየት ይላል። ይኸውም በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች እና በከፍተኛ ተቋማት መካከል የሚገኙትን በርካታ የመለያያ ነጥቦችን በማስቀመጥ መንግስታዊ ሃይማኖታዊ ኮሌጆችን እስከ መደጎም እና በመንግስታዊ ሴኩላር ኮሌጆች ውስጥ የእምነት ማካሄጃ ቦታዎችን እስከ ማመቻቸት ይፈቅዳል።

የሴኩላሪዝምን መርሕ ለበርካታ አመታት ተቀብላ
የኖረችው አሜሪካ በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች እና ኮሌጆች
ውስጥ ተማሪዎችን ከሃይማኖታዊ ተግባራት ማገድ
ይቅርና ቋሚ የጸሎት ቦታዎችን እንዲገነቡ ፈቅዳላቸው
በሰፊው እየተንቀሳቀሱ ይገኛሉ። መሰል ተግባራት
እየተከናወኑ ከሚገኙባቸው ታላላቅ ዩኒቨርሲቲዎች
መካከል የሌ፣ዱክ እና ሚዙሪ ዩኒቨርሲቲዎች ሲገኙ
ሃይማኖታዊ ተቋማት ደግሞ እጅግ በርካታ በኾኑ
ሌሎች ዩኒቨርሲቲዎችም ውስጥ ይገኛል። ከላይ ስለ
ሴኩላሪዝም የቀረበውን ሐተታ መሠረት በማድረግ
የአገራችን ሴኩላሪዝም ከተጨባጭ ሁኔታዎች አንጻር
ሁለት ዐበይት ነጥቦችን ማካተት ይኖርብናል።

1· የኢትዮጵያ ሴኩላሪዝም ለረጅም ግዜ በሰፊው ሰፍኖ
የቆየውን የተዛባ የሃይማኖቶች ግንኙነት  ማረም
የአንድን ሃይማኖት የተናጠል ኢ–ፍትሐዊ ማኅበራዊ
እና ፖለቲካዊ ጫና በማስወገድ የሃይማኖቶችን

እኩልነት ማረጋገጥ።
 2· የሴኩላሪዝምን አንጻራዊ ባሕርይ በመገንዘብ
የመንግስት እና የሃይማኖት "መነጣጠል" የኢትዮጵያን

ሃይማኖቶች ተነጻጻሪ አቅዋም ከግምት ውስጥ ያስገባ ሊሆን ያስፈልጋል።

በአጠቃላይ መልኩ የኢትዮጵያ መንግስት ሴኩላር መሆኑን ለማረጋገጥ የወጡ ሕገ መንግስት ድንጋጌዎች ከአጠቃላይ የሴኩላሪዝም ዕይታ፣ከሕገ መንግስቱ አጠቃላይ መንፈስ እና ዓላማ አንጻር እንዲሁም የአገራችንን ተጨባጭ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ሊተረጎሙ ይገባቸዋል። የመንግስት እና የሃይማኖት መለያየትን የሚደነግገውን አንቀጽ 11ንበመጥቀስ "በምንም መልኩ" ሃይማኖታዊ ተግባራትን በመንግስት የትምህርት ተቋማት ውስጥ ማካሄድ አይቻልም ወይም መንግስት ለሃይማኖት ተከታዮች የሃይማኖታቸውን ዓለማዊ ጎኖች ሊያመቻች አይችልም" ወደሚል ድምዳሜ ማምራት ትክክለኛ እና ተገቢ አይኾንም።

የሃይማኖትን በመንግስት ትምህርት ተቋማት ውስጥ መተግበርን የሚቃወሙት ወገኖች የሚያነሱት ሌላው አንቀጽ "ትምህርት ከሃይማኖት ተጽዕኖ ነጻ በሆነ መልኩ መካሄድ አለበት" የሚደነግገውን አንቀዕ

90(2)ን ነው። የሕገ መንግስቱ አርቃቂ ኮሚሽን ቃለ ጉባኤ እና የሕገ መንግስቱ አጭር ማብራሪያ (1987) እንደሚያስረዱት የአንቀጹ መንፈስ፤ ትምህርት ቤቶች ዓለማዊ በመሆናቸው የሃይማኖት ትምህርት በመደበኛ ትምህርትነት እንደማይሰጥ ፣የትምህርቱ ይዘት ከሃይማኖቶች አስተምህሮ (አስተሳሰብ) አንጻር እንደማይቀረጽ .. ወዘተ መሆኑን በግልጽ መረዳት ይቻላል።

በዚህና ሴኩላሪዝም በተለይ በትምህርት ተቋማት ውስጥ ስላለው ባሕርይ በግልጽ እንደ ተቀመጠው አንቀጾቹ በምንም መልኩ በሃይማኖታዊ አምልኮዎች ላይ የሚያነጣጥር አንድምታ እንደሌላቸው በቀላሉ መረዳት ይቻላል። በመኾኑም የተረቀቀው ደንብ በአጠቃላይ ፀረ ኢስላምና እና ከሕገ መንግስታችን ጋር እንደሚጋጭ በጽኑ እናምናለን። ሕገ መንግስታችንን የመጠበቅ ሐላፊነት ለመንግስት ተቋማት ብቻ የሚተው ሳይሆን የሁሉም ዴሞክራሲያዊ ኀይሎች ግዴታ ነው። ሙስሊሙም ወገን ለመብቱ እና ሕገ መንግስቱ መከበር የመታገል ሐላፊነት እንዳለበት ግልጽ ነው። ስለሆነም ገና ለገና በትምህርት ላይ

ችግር ሊፈጥር ይችላል በሚል ሰበብ የተማሪውን የእምነት ነጻነት ለመገደብ እየተዘጋጀ ያለውን ደንብ በሕጋዊ መንገድ መሟገት ይጠበቅብናል። ውጤቱም ከእስከ ዛሬው በተሻለ መልኩ መብቱን ማስከበር አልያም እስከ ዛሬ አስከብሮት የቆየው መብቱ እንዳይነጠቅ መጠበቅ ይሆናል ።

በመሆኑም፦ ይህንን በመገንዘብ ሶላት መስገድ ህገመንግስታዊ መብታችን በመሆኑ ትላንትም ዛሬም ሰላማዊ በሆነ መልኩ ፍቃድ እንድትሰጡን በትህትና እንጠይቃለን።

[የለቡ 2ተኛ ደረጃ ት/ት ቤት ሙስሊም ተማሪዎች]